# ጋዜጠኞች ለአገራችን የዲፕሎማሲ እድገት የበኩላቸውን ሚና እንዲጫወቱ ጥሪ ቀረበ፡፡



የኢፌዲሪ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዶ/ር ወርቅነህ ገበየሁ ጋዜጠኞች ለአገራችን የዲፕሎማሲ እድገት የበኩላቸውን ሚና እንዲጫወቱ ጥሪ አቀረቡ፡፡

ዶ/ር ወርቅነህ እንደተናገሩት፣ የኢፌዲሪ የውጭ ጉዳይና የአገራዊ ደህንነት ፖሊስና ስትራቴጂ በዋነኛነት የሚያጠነጥኑት ህዝቡ በየደረጃው ተጠቃሚ የሚሆንበት ፈጣን ልማት እና የዲሞክራሲ ግንባታን እውን ለማድረግና ለዚህ የተመቻቸ ሁኔታ ሲፈጠር ነው ፡፡

የውጭ ግንኙነት እና የዲፕሎማሲ ስራችን በመንግስት በሚደረግ ጥረት ብቻ ውጤታማ ይሆናል የሚል ብዥታ የለንም፡፡ ዶ/ር ወርቅነህ ምልዐተ ህዝቡ በተለያየ መንገድ ተሳትፎ እንዲኖረው የማድረግ ጉዳይ በጣም አስፈላጊ በመሆኑ ከመገናኛ ብዙሃን ጋር ተጠናክሮ መስራት አስፈላጊ ነው ብለዋል ፡፡

የመገናኛ ብዙሃን የመንግስትን ጉድለቶች ከማሳየት በተጨማሪ በውጭ ግኑኙነት መስክ የተስተዋሉ ስኬቶችና ውጤቶች በተገቢው ሁኔታ ለህብረተሰቡ ተንትኖ በማቅረብ ብሄራዊ መግባባት እንዲፈጠር አስተዋጽኦ የማድረግ ኃላፊነት እንዳለባቸው ገልጸዋል፡፡

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር

ቃልአቀባይ ጽ/ቤት

ሃምሌ 13 ቀን 2009 ዓ.ም